አርቲክል
በሳሮን ስማቸው

# አደገኛው ገዳይ በሽታ

በአይን በማይታዩ ተህዋስያን አማካኝነት የሚመጣ፣ አጣዳፊ ተቅማጥና ትዉከት በማስተካከል በሰዉነት ዉስጥ የሚገኝን ፈሳሽ አሚጦ በማስወጣትና አቅምን በማዳከም አፋጣኝ ህክምና ካልተደረገ በጥቂት ሰዓታት ዉስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነዉ- ኮሌራ፡፡

የኮሌራ በሽታ ዋና መተላለፊያው መንገድ በዓይነ ምድር የተበከለ ምግብ ወይም መጠጥ በተለያየ መንገድ ወደ አፍ ሲገባ ነዉ፡፡ በተህዋስያኑ የተበከለ ምግብ ወይም ዉሃ ወደ አፍ ከሚገባባቸዉ አጋጣሚዎች መካካል የተበከለ የምንጭ፣የወንዝ፣የዝናብ፣የቧንቧ፣የጉድጓድ እና የሀይቅ ዉሃን መጠቀም፤በበሽታዉ አምጪ ትሀዋሲያን የተበከሉ የዉሃ ማጠራቀሚያና መገልገያ እቃዎችን በአግባቡ አለማጽዳት፤በአግባ ባልታጠበ እጅ ምግብን ማዘጋጀትና አቅርቦ መመገብ፤በበሽታዉ አምጪ ተህዋስያን የተበከለ ምግብ፣አትክልቶችና ፍራፍሬዎችን መጠቀም፤ የኮሌራ ታማሚን ተቅማጥና ትዉከት በአግባቡ አለማስወገድ፤ክዳን የሌላቸዉንና ለዝንቦች የተጋለጡ የምግብ ማስቀመጫና መመገቢያ እቃዎችን መጠቀም፤ከኮሌራ ታማሚ ጋር ንክኪ የነበራቸዉ ቁሳቁሶችን ሳያፀዱ መልሶ መገልገል፤በኮሌራ ምክንያት ህይወቱ ያለፈ ሰዉ ጋር ጥንቃቄ የጎደለዉ ንክኪ ማድረግ ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላው ከኮሌራ በሽታ ጋር በተያያዘ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ የሽታው ዋና ዋና ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ ማወቅ ነው፡፡ በመሆኑም በድንገት የሚከሰት ብዛት ያለዉ አጣዳፊ ተቅማጥ (የሩዝ ዉሃ የመሰለ)፣በተደጋጋሚ ማስመለስ፣የሰዉነት ፈሳሽ መጠን መቀነስ፣የመገጣጠሚያ ህመም፣የድካም ስሜት፣የአፍ መድረቅ፣የቆዳ መሸብሸብ፣የዉሀ ከመጠን በላይ መጥማት እና የአይን መሰርጎድ የመሳሰሉት ምልክቶች ናቸዉ፣

“ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ” እንደሚባለው በኮሌራ በሽታ ተይዞ ከመማቀቅ በፊት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የበሽታው መከላለከያ መንገዶች ተብለው የሚወሰዱት የመፀዳጃ ቤትን ሁልጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ እጅን በወሳኝ ጊዜያት በንፁህ ዉሃና ሳሙና በሚገባ መታጠብ፣ ዉሃን አፍልቶ በማቀዝቀዝ ወይም በዉሃ ማከሚያ መድሀኒት የታከመ ዉሃ መጠቀም፣ምግብን በሚገባ አብስሎ በትኩስነቱ መመገብ፣የምግብ እቃዎችን በንፅህና መጠበቅ፣ማናቸዉንም ከቤት እንዳይበከል ጉድጓድ መቆፈር እና ማስወገድ፣ አትክልቶችንና

ፍራፍሬዎችን ከመመገብ በፊት በንጹህ ዉሃ ማጠብና ወዲያዉኑ መመገብ፣ከበሽተኛዉ ከሚወጣ ፈሳሽ ጋር ንክኪ ያላቸዉ እቃዎች እና ቦታዎች በአግባቡ ማጽዳት፣ በኮሌራ የታመመ ሰዉ ጋር ቅርርብ ወይም ንክኪ ሲኖር፣ እጅን በንጹህ ዉሃና ሳሙና በአግባቡ መታጠብ፣ ኮሌራ በሽታ መከላከያ ክትባትን መከተብ እና የበሽታዉ ምልክት የታየበትን ሰዉ ፈጥኖ ወደ ህክምና መዉሰድ ናቸው፡፡

ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተገኘው መረጃ እንደሚሳየው ከታህሳስ 24/2017 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ላይ በክልሉ በዋናነት በቋራ፣ በባህር ዳር ዙርያ፣ በጃዊ፣ በቡሬ ከተማ፣ በባህር ዳር ከተማ እና በደራ ወረዳዎች በሽታው ተከስቷል፡፡ ለወረርሽኙ መስፋፋት ዋነኛ ምክንያቶችም ብዙ የፀበልተኛ ጉዞ መኖር በተለይ (ቋራ በርሚል ቅ/ጊዮርጊስ፣ ባህር ዳር ዙርያ አንዳሳ ቅ/ጊዮርጊስ፣ ቡሬ ባጉና፣ ጃዊ ፍልዉሃ፣ ደራ ወንቅሽት ቅ/ገብርኤል የፀበል ቦታዎች) አካባቢዎች ሲሆኑ በእነዚህ የፀበል ቦታዎች በቂ የሆነ የንፁህ መጠጥ ዉሃና መጸዳጃ ቤት አለመኖር ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን በሽታ ለመቆጣጠር የቅኝት ስራውን በማጠናከር በበሽታው የተጠቁ ሰዎችን ቶሎ በመለየት ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ በበሽታው ከተጠረጠሩ ሰዎች የሰገራ ናሙና በመውሰድ ወረርሽኙ በላቦራቶሪ የማረጋገጥ፤ ወረርሽኙ በተከሰተባቸዉ ቦታዎች የዉሃ ናሙና በመዉሰድ የተበከሉ ዉሃዎች እንዲታከሙ ማድረግ፤የኮሌራ ወረርሽኝን በተመለከተ በየሳምንቱ ከዞኖች ጋር የበይነ መረብ ውይይት ተደርጓል፤ እየተደረገም ነዉ፡፡

የጥምረት ኮሚቴዎችን (የክስተት አስተዳደር ስርዓት እና የፈጣን ምላሽ ሰጪ ኮሚቴ) ወደ ስራ በማስገባት እዲሁም ከክልል እና አጋር አካላት የተቀናጀ ቡድን ተዋቅሮ በባህርዳር ከተማና በሰሜን ጎጃም ዞን ድጋፋዊ ጉብኝት ተደርጓል፡፡ አጋር ድርጅቶች በተለይ ቋራና ባህር ዳር ዙሪያ እንዲገቡና አፋጣኝ የምላሽ ስራዎች እንዲሰሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ለባለሙያዎች የኮሌራ ወረርሽኝ ቅኝት እና ምላሽ ስልጠና ተሰጥቷል ፤ጊዚያዊ የኮሌራ ህክምና ማዕከል ችግሩ በተከሰተባቸው ቦታዎች በማዘጋጀት እና ጤና ባለሙያዎችን በጊዚያዊነት በመመደብ ህክምና አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ከአጋር ድርጅቶችና ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች፤ ከሃይማኖት አባቶች ጋር ዉይይት በማካሄድ የጋራ እቅድ ተዘጋጅቶ (የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ) በድርጊት መርሃ-ግብር በመለየት መከታተል እና የክልሉ ማህበረሰብ ግንዛቤ እንዲኖረው ሚዲያዎችን በመጠቀም ስለበሽታው ወቅታዊ ሁኔታ እና ቁልፍ መልዕክቶች እንዲተላለፉ እና በሽታውን ከመከላከል ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሉች በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል እየተሰርም ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ሰው የኮሌራ በሽታ ተጠቂ እንዳይሆን ከግል ንጽህና ጀምሮ አካባቢንም ጽዱ በማድረግና ሌሉች የበሽታው መከላከያ መንገዶችን በመጠቀም በተለይም የበሽታው ስረጭት ከፍ ወዳለባቸው የጸበልና መሰል አካባቢዎች ከመሔድ በመቆጠብ በሽታን መከላከል ያስፈልጋል።